Fairfax County PUBLIC SCHOOLS
ENGAGE • INSPIRE • THRIVE

Office of ESOL Services
Instructional Services Department
8270 Willow Oaks Corporate Drive
Fairfax, Virginia 22031

የተማሪ ስም ______________________________ቀን ____________________

የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ (ELP) ደረጃ ________

ውድ ቤተሰብ(ቦች)/አሳዳጊ(ዎች):-

ልጅዎ ከተማሪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ጋር በተገናኘ በአመታዊ የእንግሊዝኛ ቋንቋ WIDA የችሎታ ግምገማ ውጤት መሰረት ከመደበኛው ትምህርቱ/ቷ በተጓዳኝ በፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤ የሚሰጡትን የትምህርት አገልግሎቶችን እያገኘ/ች ነው:: እነዚህ አገልግሎቶች ተማሪዎች ሙሉ የትምህርት ተሰጥዎአቸውን እንዲጠቀሙ ፣ ትርጉም ያለው የትምህርት ልምድ እንዲኖራቸው ይሰጣሉ:: እንዲሁም በክልሉ እና በክፍለ ከተማው በኩል የሚጠበቅባቸውን የትምህርት መመዘኛዎች እንዲያሟሉ/እንዲያልፉ ያግዛሉ::

<u>ልጅ ከዚህ በፊት ከተማረበት ትምህርት ቤት የተገኘው መረጃ የዚህን ወቅት የWIDA ACCESS for ELLs 2.0® ግምገማ ውጤት የELP ደርጃ በሚያሳይ መልኩ ከተካተተ በውጤቱ መሰረት ተስተካክሎ የELP ደርጃው ይፃፍለታል/ላታል::</u>

**የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን መለየት/መመልመል**

እንደ ኤ.አ. በ1964 በወጣው የአገር አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀፅ 5 መሰረት በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለይቶ ለማወቅ ሲሉ የተማሪዎች የቋንቋ ብቃት/ችሎታ ግምገማ እንዲያካሂዱ ይጠበቃል:: ለዚህ ብቁ ሆኖ ለመገኘት ቤተሰቦች ወይም አሳዳጊዎች በቤት ውስጥ ስለሚነገረው ቋንቋ የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፅ ሞልተው በምዝገባ ወቅት ማቅረብ ይኖርባቸዋል :: በቤት ውስጥ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ሌላ ቋንቋ ጥቅም ላይ ከዋለ ቤተሰቦች በማንኛውም የተማሪ መመዝገቢያ ጣቢያ በመገኘት ልጆቻቸው በአገር አቀፍ ደረጃ የተረጋገጠውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ መመዘኛ (ማንበብ ፣ መፃፍ ፣ ማዳመጥ ፣ መናገር) ፈተና እንዲወስዱ ማድረግ ይችላሉ:: ከእንግሊዝኛ ሌላ ቋንቋ በሚነገርበት ቤት ውስጥ ለሚኖሩ መዋለ ህፃናት/የኪንደርጋርተን ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ተማሪዎች መሆናቸውን እና መዋለ ህፃናት/የኪንደርጋርተን አገልግሎት ማግኘት እንደሚገባቸው ለመወሰን በሴፕቴምበር የWIDA ፈተና ይሰጣል:: በ1-12 ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ከአምስቱ በአንዱ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት (ELP) ደረጃዎች ይመደባሉ ::

| መዋለ ህፃናት/የኪንደርጋርተን Els | ደረጃ 1<br>አዲስ ገቢ | ደረጃ 2<br>ብቅ እያለ ያለ | ደረጃ 3<br>እያደገ ያለ | ደረጃ 4<br>እየተስፋፋ ያለ | ደረጃ 6<br>እየደረሰ ያለ |
|---|---|---|---|---|---|
| ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ የሚሰጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት (ESOL) አገልግሎት ለመቀበል ብቁ የሆነ/ች | | | | | የቀለም ትምህርት አፈፃፀም/ውጤት ለ 2 ዓመት ክትትል/ቁጥጥር የተደረገበት |

**አመታዊ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ግምገማ ውጤት**

በእያንዳንዱ የፀደይ ወራት በቨርጂንያ አመታዊ የአንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ግምገማ WIDA ACCESS ELLs 2.0® የተባለውን በK-12 ለሚገኙ የአንግሊዝኛ ተማሪዎች ይሰጣል:: በትምህርት ቤታቸው የሚገኘውን እና ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ ተማሪዎች የሚሰጠው የእንግሊዝኛ ቋንቋ አስተማሪዎች የልጆቻችሁን የማንበብ ፣ የመፃፍ ፣ የመስማት እና የመናገር ብቃት ውጤት ከናንተ ጋር አብረው ያዩታል/ይገመግሙታል:: ይህም ስለልጆቻችሁ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት ተጨማሪ መረጃ ይሰጣችኋል::

**የቋንቋ አጠቃቀም/ስርዓት ትምህርት መርሃግብር**

የቋንቋ አጠቃቀም/ስርዓት የትምህርት መርሃግብር አላማው የአንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን በእንግሊዝኛ ብቁ ሆነው እንዲገኙ እና ሌሎች ተመሳሳይ ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን ፈታኝ የብቃት መለኪያ/ማረጋገጫ ነጥቦች እንዲያሟሉ መርዳት ነው :: በእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ማሻሻያ ገብተው የሚማሩ ከደረጃ 1-4 የሚገኙ ተማሪዎች ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ ተማሪዎች የሚሰጠውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ (ESOL) አገልግሎት ያገኛሉ:: በWIDA ACCESS for ELLs® 2.0 4.4 ነጥብ ወይም ከዛ በላይ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች እንደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ (ELP) ደረጃ 6ኛ ይቆጠራሉ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቁ ተብለው ይሰየማሉ:: ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ የሚሰጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ

*የኪንደርጋርተን/ወዋእለ ህፃናት ተማሪዎች WIDA ACCESS የመመደቢያ ፈተና™ (W-APT) በሴፕቴምበር ይወስዳሉ:: በፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤት ከK-12 የሚማሩ ተማሪዎችን በዓመቱ ውስጥ WIDA የንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት መመዘኛ™ (MODEL) ወይም የWIDA ማጣሪያ ይወዳሉ::

ትምህርት (ESOL) አገልግሎት ለቀለም ትምህርት መሰረት ሲሰጥ  የእንግሊዝኛ ቋንቋ እውቀትን አንድያገኙ እና ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ልክ እንደ እኩዮቻቸው በተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ግባቸውን እንዲሙቱ ለማስቻል እንዲሁም ከክፍል መዛወር ፣ መመረቅ ፣ ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁ በመሆን የታቀደውን ግብ መምታት ለሚፈልጉ ሁሉ ተጨማሪ ድጋፍ በመስጠት መሰረት ያስይዛል:: ይህን ለማድረግ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች እድሜያቸውን ባማከለ የክፍል ደረጃ ይመደባሉ:: እንዲሁም ለቀለም ትምህርት በሚሆን ቋንቋን እና ስነጥበብን ባገናዘበ ሁኔታ በእንግሊዝኛ ሂሳብን ፣ ሳይንስን እና ህብረተሰባዊ ጉዳዮችን እንዲማሩ ይደረጋል:: ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የተዘጋጀው የማስተማሪያ ግብዓት/ቁስ ከእያንዳንዱ የትምህርት ደረጃ ጋር እንዲጣጣም ተደርጓል:: በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ያለውን ቋንቋ እና ትምህርቱ በሙሉ ከWIDA የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት ልኬት ጋር እንዲደጋገፍ ተደርጓል::

ለእያንዳንዱ ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ የሚሰጡ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት (ESOL) አገልግሎቶች የጊዜ ልዩነት አላቸው:: ለውጡን/እድገቱን ለመለካት አመቱን በሙሉ የተለያዩ ግምገማዎች/መለኪያዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ:: የግምገማው ውጤቶች የልጆቹን የግል ፍላጎት የሚያሟላ የመማሪያ መንገድ ለማዘጋጀት  በአስተማሪዎቹ ጥቅም ላይ ይውላሉ:: ተማሪዎች በቋንቋ እውቀት ግብይት ሂደት ውስጥ በራሳቸው ጊዜ ተጉዘው ለቦታው/ለደረጃው የተለየውን መስፈርት ሲያሟሉ ወደሚቀጥለው ደረጃ ይሸጋገራሉ:: በፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤ የሚገኙ አብዛኛው የእንግሊዝኛ  ቋንቋ ተማሪዎች (Els) ሆነው ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ የሚሰጠውን የእንግሊዝኛ  ቋንቋ ትምህርት (ESOL) አገልግሎት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቁ እስከሚሆኑ በአማካይ ለሶስት ዓመታት ትምሕርቱ ይሰጣል::

የዕርሶ ልጅ ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ ከሚሰጠው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ሌሎች አገልግሎቶች ለምሳሌ:- እንደ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ወይም ክፍል 504ን በሚመለከት ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ (ESOL) አገልግሎት ፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አስተማሪዎችን እና ሌሎች ተባባሪ ቡድኖችን ጨምሮ በጋራ ግለሰብ ተኮር የማስተማሪያ  መርሃግብር ወይም የ504ን አላማን ለማሳካት እቅድ ይነድፋሉ:: ይህ አገልግሎት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሆነው ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ ከሚሰጠው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር በተጓዳኝ ይሰጣል::

**የመውጫ/የማጠናቀቂያ መስፈርት**

በዓመቱ የንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ግምገማ ውጤት WIDA ACCESS for ELLs 2.0®, አንድ ተማሪ በቋንቋው ብቁ መሆኑን/ኗን እና ከዚህ በኋላ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሆነው ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ የሚሰጠውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት መውሰድ እንደማያስፈልገው/ጋት ለመወሰን ያስችላል:: አንድ ተማሪ  በእንግልዝኛ ቋንቋ ብቁ ወይም ELP 6ኛ ደረጃ ለመባል በWIDA ACCESS for ELLs 2.0® ፈተና 4.4 ነጥብ ወይም ከዛ በላይ አጠቃላይ ነጥብ ማምጣት ይኖርበታል/ባታል:: በንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ (ELP) 6ኛ ደረጃ ከደረሱ በኋላ ተማሪዎች ትርጉም ባለው መንገድ በመደበኛ የቀለም ትምህርት ሂደቱ መሳተፋቸውን ለማረጋገጥ ለቀጣዩ ሁለት አመታት ክትትል ይደረግባቸዋል::

**የሚጠበቀው የመመረቂያ ደረጃ**

የቨርጂኒያ ትምህርት ክፍል ሁሉም ተማሪዎች 9ኛ ክፍልን ከጀመሩ በኋላ በአራት አመታት ውስጥ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ እና እንዲመረቁ ይጠብቃል:: ነገር ግን የአገር አቀፉ ደንብ/አሰራር ተማሪዎች በአምስት ወይም በስድስት ዓመት ትምህርታቸውን እንዲጨርሱ እድሉን ይሰጣል:: ፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤት ሁሉንም ተማሪዎች ለማገዝ ትክክለኛ መመሪያ በመስጠት እና በቨርጂንያ 91% (ዘጠና አንድ በመቶ) የሚሆኑ ተማሪዎች በሰዓቱ እንዲመረቁ በማድረግ በጣም ተሳክቶለታል::

**የቤተሰብ መብቶች**

ቤተሰቦች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸው ለሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ የሚሰጠውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት (ESOL) አገልግሎት እንዳያገኙ የማድረግ መብት አላቸው:: *ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ የሚሰጠውን የእንግሊዝኛ  ቋንቋ ትምህርት (ESOL) አገልግሎት ልጅዎ እንዳያገኝ ለማድረግ ከወሰኑ በልጅዎ ትምህርት ቤት እና በልጅዎ የግል ማህደር ውስጥ የሚገኘውን የእምቢታ ቅፅ መሙላት ይኖርቦታል::*  አገልግሎቱ ቢቋረጥም ልጅዎ እንደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ ይቆጠራል/ትቆጠራለች እናም በአገር አቀፍ ሕግ/ድንጋጌ መሰረት በየዓመቱ በሚደረገው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ELP Level 6 ደርሶ/ሳ በእንግሊዝኛ ብቁ አስከሚሆን/ምትሆን  ድረስ WIDA ACCESS ለ ELLs 2.0® ግምገማ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ ይደረጋል:: ቤተሰቦች/አሳዳጊዎች ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ የሚሰጠውን የእንግሊዝኛ  ቋንቋ ትምህርት አገልግሎት (ESOL)  በማንኛውም የትምህርት ወቅት እንደገና መጠየቅ ይችላሉ::

ስለ ልጅዎ ለውጥ/እድገት ወይም ስለ ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ የሚሰጠውን የእንግሊዝኛ  ቋንቋ ትምህርት አገልግሎት (ESOL) መረጃ ከፈለጉ እባክዎ ትምህርት ቤት የሚገኘውን የልጅዎን አስተማሪ ያነጋግሩ:: ለልጅዎ ትምህርት ስላሎት የማያሰልስ/ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እናመሰግንዎታለን:: ልጅዎ የቀለም ትምህርቱን/ቷን በሚመለከት በተሟላ መልኩ ስኬታማ እንዲሆን/ትሆን ለመርዳት ከርሶ ጋር ለመስራት እንመኛለን::

ከልብ



Rich Pollio
የESOL አገልግሎት ዳይሬክተር መኮንን